# <u>በጥቂት የአፈንጋጭ ቡድን ደጋፊዎች ሳቢያ የአገር ወዳዶች ትግልና አስተዋጽኦ አይሸፈንም፤ ለትግሉም ድጋፋችን ይቀጥላል</u>

## ከቫንኮቨር የቅንጅት ደጋፊዎች የተሰጠ መግለጫ

**ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ (Kinjit Ethiopian Cultural and Relief Organization in Toronto) "እራስህን እወቅ" በሚል ርዕስ በጄንዋሪ 4 ቀን 2008 ዓ.ም የቫንኮቨር ቅንጅት ድጋፍ ነኝ ለሚለው ቡድን አፍራሽ ድርጊቱን በማውገዝ የሰጠው መግለጫ ትክክለኛና የምንደግፈው ነው::**

**በእነዚህ የቅንጅትን መስመር ስተው በሚጓዙ በጥቂት የአፈንጋጩ ቡድን ደጋፊ ግለሰቦች ምክንያት መላውን በቫንኮቨር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵውያንን ለትግሉ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ለይቶ በመግለጫው ላይ በግልጽ ባለመቀመጡ ከውጭ ሆኖ ለሚመለከተው ወገን የቫንኮቨር ነዋሪዎች አስተዋጽኦ በመሸፈኑና ያልተብራሩ ጉዳዮች በመኖራቸው ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ ይህንን መግለጫ በቫንኮቨር የምንገኝ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን አውጥተናል::**

**በመጀመሪያ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ በቫንኮቨር ከመቋቋሙ በፊት ቅድመ ግንቦት 1997 ምርጫ ለተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎች ምርጫ ዝግጅት አቅሙ የፈቀደውን የገንዘብና የሞራል ድጋፍ አድርጓል:: ከምርጫ ቀጥሎ የወያኔ አጋዚ የተባለውን አረመኔ ሠራዊቱን ባልታጠቁ ሕፃናት፣ ሴቶች፣ ሽማግሌና አሮጊቶች ላይ አዝምቶ ባደረገው ሁለት ዙር የጭፍጨፋ ተግባር ተቆጥቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተዋቀሩት የኢትዮጵያውያን ጋር እየተባበርን ትግሉ የጠየቀውን ሁሉ ሲያከናወን ቆይቷል::  የሚች ቤተሰቦችን አጽናንቷል ጠይቋል:: ገንዘብ አሰባስቦ በቀጥታ ለቅንጅት ጽህፈት ቤት በባንክ አካንውንት ገቢ አድርጓል:: እንዲሁም የቫንኮቨር ሕዝብ የትግሉን ቀጣይነት በመገንዘብ በመጠባበቂያነትም ገንዘብ አዋጥቷል:: ሌሎችም በርከታ ጉዳዮችን አከናውኗል::**

**ይህ በዚህ እንዳለ በወቅቱ ሲያስተባብር የነበረው ኮሚቴ ሕጋዊ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ እንዲቋቋም ከዋናው የሰሜን አሜሪካን አስተባባሪ ጋር እንዲሁም ከቶሮንቶ ጽህፈት ቤት ጋር ግንኙነት አድርጎ የነበረ ቢሆንም፤ እውነተኛና ሀቀኛ ሰዎች መስለው ጥቂት አስመሳዮች በኮሚቴ ውስጥ ገብተው የቅንጅትን መንፈስና አሰራር ሳይሆን የአፈንጋጩ ቡድንን  ዓላማ ለማካሄድ ችለዋል::  እነዚሁ የእነአንዳርጋቸው ቡድን ሰዎችና ለዚሁ የተንኮል ተግባር የተመለመሉ ግለሰቦች በአንዳርጋቸው ፅጌ ተወክለናል በማለት "በሲቪክ ኢንስቲቲዩሽንና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ለቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴነት መምረጥም ሆነ መመረጥ አይችሉም" የሚል መመሪያ አለ በማለት ግማሹን በማግለል ጥቂቱን በማቀፍ የተመሠረተ ስለነበር ይህንንም በወቅቱ አሳውቀን መልስ አላገኘንም:: ድጋፍ ድርጅቱ ሲቋቋም በአንዳርጋችው ፅጌ ተወክያለሁ ያሉት በተለይ ከካልጋሪ የመጡት አደራጅ "እኔ የቅንጅት አባል ድርጅት አባል ነኝ" በሚል የተሳሳተ መረጃ በመስጠት በቅንጅት ስም ሌሎችን የማግለል ተግባርም ፈጽመዋል:: የዚህን ዓይነት አሰራርና አፍራሽ ሂደት የተረዱም እራሳቸውን አግልለዋል::**

**ይህ በቅንጅት ሥም ከደረሱት ጥቂት በዐይን ከሚታዩ ጥፋቶች ለመጥቀስ ያህል፤**

1. **ከወያኔ ጋር በመተባበር የሚሊኒየም ዝግጅት በቫንኮቨር ሲዘጋጅ ከአንድነት ኃይሎች ከመተባበር ይልቅ በተቀራኒ ከተሰለፉት ጋር በመሆን ሲጎዳን የነበረ ነው::**
2. **በአከባቢየችን የሚገኙ የወያኔ ድርጅቶችን ፊት ለፊት በማጠናከር ላይ ይገኛል::**
3. **በሚሊኒየም በዓል ላይ የሰብዓዊ መብት ታጋዮች በበዓሉ ላይ ተገኝተው ንግግር እዳያደርጉ ከፀረ አንድነት ኃይሎች ጋር በታኝ ቅስቀሳ በማድረግ ለአባንግ ሜቶ የአይሮፕላን ትኬት ከተከፈለ በኋላ አስቀርቶታል::**

**ከላይ የተጠቀሱት በአጭሩ ለአብነት እንጂ በርከታ ጥፋቶች እደረሱ ነው::  አሁን ደግሞ የቅንጅት ፕሬዚዳንት ክቡር ኤንጂኔር ኃይሉ ሻዉል ታሕሣሥ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ያወጡትን መግለጫ በመቃወም ያወጡት መግለጫ ከ5 እስከ 10 የማይበልጡ የአንዳርጋቸው ወኪሎች እንጂ የቫንኮቨርን ሕዝብ ሊወክሉ የማይችሉ መሆኑን እንገልጻለን::**

**ቫንኮቨር፤ ካናዳ**
**ጄንዋሪ 16 ቀን 2008**